መልእክት ዘጠኝ

**ድል የሚነሡት በኩራት የሚከተሉት በግ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ራእ. 14፥1-5፤
ዘፍ. 5፥22-24፤ ዕብ. 11፥5-6፤ ማቴ. 24፥45-51

**I. ራእይ 14፥1-5 ድል የሚነሡት በኩራት እንደሚከተሉት በግ ክርስቶስን ይገልጣል፦**

ሀ. በኩራቱ በእግዚአብሔር እርሻ ውስጥ ቀድመው የሚበስሉት በሕይወት ያሉት ድል ነሺዎች ናቸው፤ ስለዚህ ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኩራት እንዲሆኑ ከመከሩ በፊት ይታጨዳሉ፦

1. በኩራቱ በእግዚአብሔርና በክርስቶስ መገኘት ውስጥ ለመሆን ወደ ሰማያዊው ጽዮን ተራራ፣ በሦስተኛው ሰማይ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ይነጠቃሉ።
2. የመነጠቅ ትርጉም ወደ ጌታ መገኘት ውስጥ መወሰድ ማለት ነው፤ ወደ ጌታ መገኘት ውስጥ ለመወሰድ፣ ዛሬ በመገኘቱ ውስጥ መሆን አለብን—ሉቃ. 21፥36፤ 2 ቆሮ. 2፥10፤ ሆሴ. 6፥2፤ 2 ጢሞ. 4፥8፤ ሐዋ. 26፥16።
3. መነጠቅ ጠላትን ለማሸነፍ እና እግዚአብሔርን ለማርካት ነው፤ ጌታ ከጠላቱ ጋር እንዲዋጋ ወንዱ-ልጅ ያስፈልገዋል፣ ነገር ግን ለእርካታው እና ለደስታው በኩራቱ ይበልጥ ያስፈልጉታል—ራእ. 12፥5፤ 14፥1፣ 4።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መነጠቅ ሁለት ገጽታዎችን ይገልጣል፤ ከታላቁ በመከራ በፊት የድል ነሺዎቹ መነጠቅ እና በታላቁ መከራ መጨረሻ የብዙሃኑ አማኞች መነጠቅ—ማቴ. 24፥40-41፤ ሉቃ. 21፥36፤ ራእ. 3፥10፤ 1 ተሰ. 4፥15-17፤ ራእ. 12፥5፤ 14፥1።

ሐ. በዘሌዋውያን 23፥10 የመነጠቅን ምሳሌ—በእርሻ ላይ የሰብሉን ሙብሰል ምሳሌ—እናያለን—ማቴ. 13፥24፤ ራእ. 14፥14-16፦

1. መነጠቅ ብለን የምንጠራው የእግዚአብሔርን ሰብል መታጨድ ነው፤ ይህ አጨዳ የሚያመለክተው አማኞች ከምድር እንደሚወሰዱ ነው—ማቴ. 13፥30፣ 39።
2. የሰብሉ ክፍል—በኩራቱ—ቀደም ብለው ይበስላሉ፣ ቀደም ብለውም ይታጨዳሉ፤ የተቀረው ሰብል—መከሩ—ዘግይቶ ይበስላል፣ ዘግይቶም ይታጨዳል።
3. በራእይ 14 መሠረት፣ ሁለት የመነጠቅ ዓይነቶች አሉ—የበኩራቱ መነጠቅ እና የመከሩ መነጠቅ—ቁ. 4፣ 14-16።

መ. በኩራቱ ለእግዚአብሔር እንደሆነ ትኩስ ድሰታ በጽዮን ወዳለው የእግዚአብሔር ቤት ይነጠቃሉ፤ ይህ ለእግዚአብሔር እርካታ ነው—ዘጸ. 23፥19፤ ዘሌ. 23፥10፤ ተዛ. ዮሐ. 20፥17።

ሠ. በኩራቱ የበጉ ስምና የአባቱ ስም በግምባራቸው ላይ ተጽፎአል፤ ይህ ከበጉና ከአብ ጋር አንድ የመሆናቸው እና የእነርሱ የመሆናቸው ምልክት ነው—ራእ. 14፥1።

ረ. በኩራቱ ከእግዚአብሔር ሰብል መካከል ብስለት ላይ ለመድረስ የመጀመሪያዎቹ ናቸው—ዕብ. 5፥14—6፥1፤ 1 ቆሮ. 2፥6፤ ኤፌ. 4፥13፤ ፊልጵ. 3፥15፦

1. መለወጥ በተፈጥሮአዊው ሕይወታችን መለወጥ ነው፤ ሙብሰል በሚለውጠን መለኮታዊ ሕይወት መሞላት ነው—ሮሜ 12፥2፤ ኤፌ. 3፥19።
2. ለእግዚአብሔር መገለጥ ብስለት ያስፈልጋል፤ የእግዚአብሔርን መልክ መያዝና ሥልጣኑን ማንቀሳቀስ የሚችለው የበሰለ ሕይወት ብቻ ነው—ዘፍ. 1፥26፤ ሮሜ 5፥10፣ 17፣ 21።

**II. በጉን እንድንከተለው እና በኩራት እንሆን ዘንድና እስከ ብስለት እንቀጥል ዘንድ፣ ሞትን ለማምለጥ እና እግዚአብሔርን ደስ የማሰኘትን ምስክርነት ለማግኘት በእምነት አካሄዳችንን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ አለብን፦**

ሀ. ሞትን ለማምለጥ እና እግዚአብሔርን ደስ የማሰኘትን ምስክርነት ለማግኘት መንገዱ አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ነው—ዘፍ. 5፥22-24፤ ዕብ. 11፥5-6፦

1. አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ማለት እግዚአብሐርን አለመቅደም፣ ደፋር አለመሆን፣ ነገሮችን በራሳችን ፅንሰ-ሃሳብና መሻት መሠረት አለማድረግ፣ ነገሮችን በዘመኑ አዝማሚያ መሠረት አለማድረግ እና ያለ እግዚአብሔር ምንም ነገር አለማድረግ ማለት ነው—ተዛ. መዝ. 19፥12-13፤ ኢያ. 9፥14፤ ሉቃ. 24፥15።

2. አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ማለት እርሱን እንደ ማዕከላችን እና እንደ ሁሉ ነገራችን መውሰድ፣ በእግዚአብሔር መሠረትና ከእግዚአብሔር ጋር፣ በመገለጡ እና በምሪቱ መሠረት መኖር እና ነገሮችን ማድረግ እና ሁሉንም ነገር ከእርሱ ጋር ማድረግ ማለት ነው—ሮሜ 8፥4፣ 13-14፤ ገላ. 2፥2፤ 2 ቆሮ. 5፥14-15።
3. አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ማለት ክርስቶስ ራሱ በሆነው በማይሞተው ሕይወት እንጂ እኛ በሆንነው ወይም ማድረግ በምንችለው አንኖርም ማለት ነው—ቁ. 4፣ 9።
4. አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር የማይቋረጥ ኅብረት ማድረግ፣ ከጌታ ጋር በማያቋርጥ ግንኙነት ውስጥ መሆን እና በማያቋርጥ መስረጹ ውስጥ መሆን ማለት ነው—1 ዮሐ. 1፥3፤ ፊልጵ. 4፥6፤ 2 ቆሮ. 3፥16፣ 18።
5. አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ማለት የተባረከውን ሥላሴ ለመደሰት መንፈሳችንን ያለማቋረጥ ማንቀሳቀስ ማለት ነው—ይሁዳ 14፣ 19-21።
6. አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ከእርሱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እኔነታችንን እና ከእኔነታችን የሆነውን ነገር ሁሉ መካድን ያመለክታል፤ ራሳችንን ለእርሱ እንደሰጠን፣ ለእርሱ እንደምንሸነፍና እርሱ እንዲመራ እንደምንፈቅድ ያመለክታል—ማቴ. 16፥24-25፤ 2 ቆሮ. 2፥13-14።

ለ. አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ በእምነት መመላለስ ነው—5፥7፤ ዕብ. 11፥5-6፦
1. እምነት ማለት እግዚአብሔር ["እኔ ነኝ"] እንደሆነ እናምናለን ማለት ነው—ቁ. 1-2፣ 6፤ 2 ቆሮ. 4፥13፣ 18፦
ሀ. ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት፣ እግዚአብሔርን ደስተኛ ማድረግ አይቻልም—ዕብ. 11፥6።
ለ. እግዚአብሔር ["እኔ ነኝ"] እንደሆነ ማመን፣ እርሱ ለእኛ ሁሉ ነገር እንደሆነ እና እኛ ምንም እንደሆንን ማመን ነው—ዮሐ. 8፥58፤ መክ. 1፥2።
ሐ. እግዚአብሔር ["እኔ ነኝ"] እንደሆነ ማመን እኛ እንዳልሆንን ያመለክታል፤ በሁሉም ነገር እርሱ ብቸኛው፣ ልዩና ብቸኛው ["እኔ ነኝ"] መሆን አለበት፣ እኛ ደግሞ በሁሉም ነገር ምንም መሆን አለብን—ዘፍ. 5፥24፤ ዕብ. 11፥5።
መ. እግዚአብሔር እንደሆነ ማመን፣ ራሳችንን መካድ ነው፤ በመላው አጽናፍ ዓለም እርሱ ["እኔ ነኝ"] ነው፣ እኛ ሁላችን ደግሞ ምንም ነን—ሉቃ. 9፥23።
ሠ. እኔ ምንም መሆን የለብኝም፤ መኖር የለብኝም፤ እርሱ ብቻ መኖር አለበት—ከእንግዲህ እኔ አይደለሁም፣ ነገር ግን ክርስቶስ ነው—ገላ. 2፥20።
ረ. የጠርሴሱ ሳውል በጌታ ባመነ ጊዜ፣ ጌታ "እኔ ኢየሱስ ነኝ" ብሎ ነገረው—ሐዋ. 9፥5፦
1) ጌታ "እኔ ታላቁ እኔ ነኝ፤ እኔ እኔ ነኝ፤ እኔ ["እኔ ነኝ"] እንደሆንሁ እና አንተ እንዳልሆንህ ማመን አለብህ" እያለው ነበር።
2) በመጨረሻም፣ ሳውል አብቅቶ፣ ጳውሎስ መጣ—13፥9።
ሰ. እምነት ይህ ነው—"ምንም የሌለው፣ ምንም የሆነ፣ ምንም የማያይ የመሆን፣ ነገር ግን በክብር ያለውን ክርስቶስ የሚያይ፣ በዚህ ላለው ፍላጎቶቹ እንጂ ስለምንም ግድ የማይሰኝ የመሆን አ ደስታ"—ጄ. ኤን. ዳርቢ።
2. እምነት ማለት እግዚአብሔር በትጋት ለሚፈልጉት ዋጋ እንደሚሰጥ እናምናለን ማለት ነው—ዕብ. 11፥6፤ ዘፍ. 15፥1፤ ፊልጵ. 3፥8፣ 14፦
ሀ. የሄኖክ ሽልማት ከፍተኛው የሕይወት ደረጃ—ከሞት ማምለጥ—ነበር—ዕብ. 11፥5፤ 2 ቆሮ. 5፥4፤ ሮሜ 8፥6፣ 10-11፤ 5፥17።
ለ. ጌታ ዋጋ የሚሰጥ ነው፣ እኛ ደግሞ እርሱን የምንፈልግ መሆን አለብን—መዝ. 27፥4፣ 8፤ 42፥1-2፤ 43፥4፤ 73፥25፤ 119፥2፣ 10።

ሐ. ሄኖክ፣ እንደ የመጀመሪያው የተነጠቀ ሰው፣ በሕይወት እያሉ የሚነጠቁት ድል ነሺዎች ሁሉ ወኪል ነው—ማቴ. 24፥37-51፤ ራእ. 14፥1፤ ሉቃ. 21፥34-36፦
1. መነጠቃችን አካሄዳችንን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ በመለኮታዊው ሕይወት በመብሰላችን ላይ ይመረኮዛል—ዕብ. 6፥1።
2. ሄኖክ እግዚአብሔር ስለወሰደው እስከማይገኝ ድረስ በእያንዳንዱ ቀን ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ በመቅረብና ይበልጥ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ በመሆን ለሦስት ምዕተ ዓመታት ቀንና ሌሊት ያለማቋረጥ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ዕርገት አቀና—ዘፍ. 5፥24፤ ተዛ. ጥቅስ መኃ. 8፥5።

III. **በጉን እንድንከተለው እና በኩራት ለመሆን እስከ ብስለት ለመቀጠል፣ በሚመጣው መንግሥት ክርስቶስን እንደ ሽልማታችን እንድንቀበል እግዚአብሔርን ለቤተሰቡ አባላት እንደ ምግብ ለማቅረብ ጌታ በሰጠን ተልእኮ በአገልግሎት ታማኝ መሆን አለብን—ማቴ. 24፥45-51፡-**

ሀ. እግዚአብሔር ቤተሰብ እና ለመገለጡ ራሱን ለቤተሰቡ አባላት እንደ ምግብ ለማደል የቤተሰብ አስተዳደር፣ ኢኮኖሚ አለው—1 ጢሞ. 1፥4፤ 3፥15፤ ኤፌ. 2፥19።

ለ. እግዚአብሔር ለሕዝቡ በተገቢው ጊዜ ምግብ እንዲሰጡ ታማኝና ልባም ባሪያዎችን፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች፣ መጋቢዎች፣ የአቅርቦት መተላለፊያዎች አድርጎ በቤተሰቡ ላይ ሾሟል—ማቴ. 24፥45፤ 1 ቆሮ. 9፥17፤ ኤፌ. 3፥2፤ 1 ቆሮ. 4፥1፤ 1 ጴጥ. 4፥10፤ ፊልጵ. 1፥25።

ሐ. *ምግባቸውን...ይሰጣቸው ዘንድ* የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቃልና ክርስቶስን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉ አማኞች እንደ የሕይወት አቅርቦት ማገልገልን ነው፤ ክርስቶስ ሕይወትን እንደሚሰጠው መንፈስ፣ በሕይወት ቃል ውስጥ አካል የለበሰ እና እውን የሆነ ምግባችን ነው—ዮሐ. 6፥57፣ 63፣ 68፤ ሐዋ. 5፥20፡-

1. ሌሎችን መመገብ እንችል ዘንድ ጌታን እንደ መንፈሳዊ ምግባችን ለመደሰት፣ ቃሉን በጥንቃቄ በማጤን እየቀመስነው እና እየተደሰትነው መጸለይ እና ማሰላሰል አለብን—ኤፌ. 6፥17-18፤ መዝ. 119፥15፤ ሕዝ. 3፥1-4።
2. ለጸሎት እና ለቃሉ አገልግሎት ራሳችንን መስጠት አለብን—ሐዋ. 6፥4፤ 2 ቆሮ. 3፥6፣ 8፤ ዮሐ. 7፥37-39፤ ተዛ. ዕብ. 7፥25፤ 8፥2።

መ. በልባችን ጌታችን እስኪመጣ ይዘገያል ማለት የአሁኑን ክፉ ዓለም መውደድ እና የጌታን መገለጥ አለመውደድ ነው—ማቴ. 24፥48፤ 2 ጢሞ. 4፥8፣ 10፤ ተዛ. ሐዋ. 26፥16፡-

1. ለራሳችን ገንዘብ ባለማከማቸት፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ባለጠጋ በመሆን ከመጎምጀት መጠንቀቅ አለብን—ሉቃ. 12፥15-20፤ 2 ቆሮ. 6፥10፤ ኤፌ. 3፥8።
2. "የሎጥን ሚስት አስብአት" የሚለው ዓለምን ለሚወዱ አማኞች ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ነው—ሉቃ. 17፥31-32፤ ተዛ. ሮሜ 1፥21፣ 25።
3. የጌታ መምጣት ቀን እንደ ወጥመድ በድንገት እንዳይመጣብን የነቃንና እና ተግተን የምንጸልይ መሆን አለብን—ሉቃ. 21፥34-36፤ ተዛ. ማቴ. 2፥3።

ሠ. ባልንጀሮቻችንን የሆኑትን ባሪያዎች መምታት የእምነት ባልንጀሮቻችንን መበደል ነው—24፥49፤ 18፥3-7፤ ሐዋ. 9፥4፡-

1. በእምነት ባልንጀሮቻችን ላይ መፍረድና እነርሱን መኮነን የለብንም፣ ነገር ግን ለእነርሱ ደግ፣ ርኅሩኅ መሆን፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳለን እነርሱን ይቅር ማለት አለብን—ሉቃ. 6፥37፤ ኤፌ. 4፥31-32።
2. ወንድሞቻችንን መንቀፍ ወይም መተቸት ሳይሆን ከእኛ ይልቅ የተሻሉ እንደሆኑ መቁጠር አለብን—1 ቆሮ. 6፥10፤ ፊልጵ. 2፥2-3፣ 29፡-
   ሀ. ወንድምን መንቀፍ እርሱን መተቸት ወይም በሚጎዱ ቃላት እርሱን በማመናጨቅ ማዋረድ ነው—ተዛ. ሉቃ. 17፥2።
   ለ. የነቀፋን ቃላት የሚያዳምጡት የነቀፋን ቃላት እንደሚናገሩት ተመሳሳይ ኃላፊነትን ይሸከማሉ፤ እንዲህ ያሉ ቃላት አካሉን ይጎዳሉ።
   ሐ. በተፈጥሯቸው ሌሎችን መተቸት ለሚወዱ እግዚአብሔር ሥልጣንን ፈጽሞ አይሰጣቸውም።
3. በእምነት ባልንጀሮቻችንን ላይ በኃይል መግዛት ሳይሆን ከሞት በተነሣው ክርስቶስ ሕይወትን እንደሚሰጥው መንፈስ ለመመገብ እንደ ባሪያ እነርሱን ማገልገል አለብን—1 ጴጥ. 5፥3፤ ማቴ. 20፥25-28፡-
   ሀ. አንድ ሰው በቅዱሳን ላይ በኃይል መግዛቱ ማለት ለእነርሱ ውሳኔ በመወሰን ወይም ወዴት መሄድ እንዳለባቸው በመንገር፣ ከዚህም የተነሣ የክርስቶስን ራስነት እና ጌትነት ባለማክበር ጌታን በሕይወታቸው መተካት ማለት ነው።
   ለ. ሌሎች እንዲጸልዩ፣ የጌታን ምሪት እንዲፈልጉና በአካሉ ውስጥ ተገቢውን ኅብረት እንዲያደርጉ ሳናበረታታቸው የት መሄድ እንዳለባቸው ከነገርናቸው፣ ይህ ለጌታ ትልቅ ስድብ ነው!

ረ. ከሰካሮች ጋር መብላትና መጠጣት በዓለማዊ ነገሮች ከሰከሩ ከዓለማዊ ሰዎች ጋር መወዳጀት ነው—24፥49፤ ተዛ. ኤፌ. 5፥18፡-

1. አማኞች ከመለኮታዊ ባሕርያቸውና ቅዱስ ከሆነው መቆሚያቸው የተነሣ፣ ከማያምኑ ጋር አብረው መጠመድ የለባቸውም፤ ይህ በጋብቻ እና በንግድ ሥራ ላይ ብቻ ሳይሆን በአማኞች እና በማያምኑ መካከል ባሉ የቅርብ ግንኙነቶች ሁሉ ላይ ሊተገበር ይገባል—2 ቆሮ. 6፥14፤ 1 ቆሮ. 15፥33፤ ተዛ. ምሳ. 13፥20።
2. የጎልማሳነትን ምኞት መሸሽ እና በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋር ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ መከታተል አለብን—2 ጢሞ. 2፥22።

*© 2025 Living Stream Ministry*